የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፪
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 42
ADDIS ABABA 30th June, 2009

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፭/፪ሺ፩ ዓ.ም

የአፍሪካና አውሮእስያ ስደተኛ የውኃ አእዋፋትን ዝርያ ለመጠበቅ የተፈረመውን ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፬ሺ፯፻፵

**<u>CONTENTS</u>**

**Proclamation No. 635/2009**

African-Eurasian Migratory Water Birds Agreement Ratification Proclamation Page 4740

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፭/፪ሺ፩

## <u>የአፍሪካና አውሮእስያ ስደተኛ የውኃ አእዋፋት ስምምነትን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

በአፍሪካና አውሮእስያ ስደተኛ የውኃ የአእዋፋት ዝርያን ለመጠበቅ እ.ኤ.አ. ጁን ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፭ በኒዘርላንድ አገር በሄግ ከተማ ተፈርሞ ከኖቬምበር ፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ጀምሮ በብዙ አገራት በመተ ግበር ላይ በመሆኑ፣

በዚህም የስምምነት አንቀፅ ፲፫/፫/ እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር ፩ ፲፱፻፺፱ በኋላ አባል ለመሆን ፈቃደኛ የሆኑ አገራት ስምምነቱን በማፅደቅ አባል ለመሆን ስለሚችሉ፣

ስምምነቱም በአፍሪካና በአውሮእስያ ስደተኛ የውኃ የአእዋፋት ዝርያን በአባል አገራት ትብብር ለመጠበቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚኖረው በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክ ራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 635/2009

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT FOR CONSERVATION OF AFRICAN EURASIAN MIGRATORY WATER BIRDS

**WHEREAS,** the Agreement for the Conservation of African-Eurasian Migratory Water Bird Agreement signed in Haig Netherlands on June 16/1995 was came in to force on November 1 1999;

**WHEREAS,** pursuant to Article 13(3) of the Agreement after November 1, 1999 states may become parties to the Agreement by accession;

**WHEREAS,** the agreement is found to have paramount importance in conserving the migratory water bird species through cooperation of member states;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representa-tives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 4th day of June, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአፍሪካና የአውሮእስያ ስደተኛ የውኃ አእዋፋትን ዝርያ ለመጠበቅ የተፈረመውን ስምም ነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፭/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

የአፍሪካና አውሮእስያ የውኃ አእዋፋትን ዝርያ ለመጠበቅ እ.ኤ.አ. ጁን ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፭ በሄግ ኒዘርላንድ የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የማስፈጸም ሥልጣን

የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን አግባብ ካላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥታዊ አካላት፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከህብረተሰቡ ጋር በመተባበር ስምምነቱን በሥራ ላይ የማዋልና አፈፃፀሙን የመከታተል ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Agreement for Conservation of African Eurasian Migratory Water Birds Ratification Proclamation No. 635/2009".

## 2. Ratification of the Convention

The Agreement for the Conservation of African Eurasian Migratory Water Birds, signed on the June 16th 1995, is hereby ratified.

## 3. Power of Implementation

The Ethiopian Wildlife Conservation Authority is hereby empowered to undertake all acts necessary to the implementation of the Agreement in cooperation with concerned Federal and Regional Government Organs and non-governmental organization as well as communities.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 30th day of June, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**